# የአብዮተኞች ዘመን የፍጻሜ ደወል

*የማይነጋ ህልም ሳልም*
*የማይድን በሽታ ሳከም*
*የማያድግ ችግኝ ሳርም*
*የሰው ህይወት ስከረክም*
*እኔ ለእኔ ኖሬ አላውቅም*

*ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን*

የ1960ዎቹ ና 70ዎቹ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ከማርክሲዝም አብዮታዊ ቲዎሪ ጋር ከተዋወቀና በርዕዮት አለሙ ከተቀረጸ በሀዋላ በኢትዮጵያ አዲስ የፖለቲካ ምእራፍ ይከፈታል። ይህም የፖለቲካ ምእራፍ የግራ ፖለቲካ የነገሰበትና ከሱም ጋር አብረው በሚሰርጹት የስነ ልቡናና የፖለቲካ ባህል እሴቶች የተቀረጸው የ "ያ ትውልድ" አብዮታዊው ኢሊት የፖለቲካ ምህዳሩን የጥፋት ጦር ሜዳ አድርጎት የዘለቀበት የአብዮት ዘመን ሲሆን የዚህ ዘመን ርቀትም አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ የረዘመ ነው።

በዛ በዋዜማው ወቅት የአብዮተኞች ዘመን መግባቱን ነጋሪት ከጎሰሙትና አቅጣጫውንም ከቀየሱት መሃል ዋለልኝ መኮንን አንዱ ሲሆን የአዲሱን ዘመን ግብዓትም በ1961 ዓ.ም ባቀረበው ጦማሩ (የዋለልኝ ማንፌስቶ) መንገዱን አመላክትዋል።

በዲያሌክቲክስ የእድገት ህግ መሰረት ሁሉም ነገር ከ - እስከ ገደብ አለውና እነሆ ከግማሽ ምእተ አመት በሁዋላ እድሜውንና አቅመ ፍጃታውን ጨርሶ ከአዲሱ የፖለቲካ ነባራዊ ሁኔታ ጋር መራመድ ስላልቻለ የአብዮተኞች ዘመን የፍጻሜ ደወል በመደወል ላይ ይገኛል።

ጎላ ብለው በቅርቡ ከሰማናቸው አብሳሪ ደወሎች መሃከል የፕሮፌሰር መሳይ ከበደ እንደ ወትሮው ስል እይታውን ያካፈለበት "A prescription for the political stalemate in Ethiopia" በሚል ርእስ የቀረበው ጽሁፍ ነው።

በዝርዝር ጉዳዮች ውስጥ ጥያቄ ሊያስነሱ የሚችሉ ነጥቦች ሊኖሩት እንደሚችል ታሳቢ ሆኖ ጥቅል መልእክቱ ግን የኢትዮጵያ ፖለቲካ አዲስ እመርታዊ ደረጃ ላይ መድረሱን የሚጠቁምና በድሮው ቀኖና፤ እመለካከትና አቀራረብ መቀጠል መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል ያበከረበት አዲስ ምርጥ ስራው ነው።

ፕሮፌሰር መሳይ በጽሁፉ መግቢያ ላይ ይህ የግል አስተያየቴን የገለጽኩበት ማንፌስቶ ነው ይበል እንጂ በርግጥ ያቀረበው የዘመኑን ማንፌስቶ ነው። ይህ የሃያ አንደኛው ክፍል ዘመን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምህዳር ማንፌስቶ ነው። ይህ የዋለልኝ መኮንን አብዮታዊ ማንፌስቶን የሚተካ የአዲሱ ትውልድ የፖለቲካ ማንፌስቶ ነው።

የመሳይ ማንፌስቶ በሚቀጥሉት አመታትና አስርተ-አመታት የኢትዮጵያን ፖለቲካ የሂደት አቅጣጫ ያመላከተ፤ ከገዥው ፓርቲ አንስቶ በተለያየ ጎራ የተሰለፉና ተጻራሪ የአመለካከት እምነቶችን የምያራምዱ የፖለቲካ ቡድኖች ፓርቲዎችና ግለሰቦች በጥቅሉ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር አካሎች ነን ብለው የሚያምኑ ወገኖች ሁሉ ለሚያካሂዱት የውይይት መስተጋብርና የርስ በርስ ግንኙነቶች ማሰሪያና ማቀፊያ (famework) ነው።

የጠቅላላ የጽሁፉ ይዘትም በአንድ አረፍተ- ነገር ሲቅዋጭ እንደሚከተለው አስቀምጦታል።

> " ... The point is that the movement toward greater democratization begins, no more through the overthrow of a ruling elite, but through a formula of power-sharing and the building of trust among various elite groups".

ይህ የአዲሱ ዘመን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር የሚዋቀርበት የንድፈ ሃሳብ ምሶሶ ነው። ዲሞክራሲ ማለት ከሁሉም በላይ ልዩነቶችንና የጥቅም ግጭቶችን በስልጡንነት (civilized) በሆነ መንገድ ማስተናገድና በሰላማዊ መንገድና በመከባበር የመረሩና የከረሩ ቅራኔዎችን መፍታት ማለት ነው።

ባለፈው ሃምሳ አመት የበቀለውን የኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ባህልን (ዋለልኝዝምን) ለወረሰውና በውስጡ እንዲያልፍ ለተገደደው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኢሊት ይህ አዲስ የፖለቲካ አቅጣጫ የማይወጣ የሰማይ ዳገት መስሎ ቢታየው ሊያስደንቅ አይገባም። ለአዲሱ ትውልድ ግን በደስታ የሚንደረደረው የአዲስ ዘመን ጎዳና ይሆናል።

አይነ-ህሊናን ከሚጋርደው የጥላቻና የጠላትነት የስነ-ልቡና ቅርስ ተረማምዶ ከዚህ የአስተሳሰብ አዲስ ጎዳና ለመቀላቀልና እኩል ከጊዜው ጋር ለመራመድ በራስ ላይ ተሃድሶ ማድረግን ይጠይቃል። ምክንያታዊና ተግባራዊ ለሆነ የአስተሳሰብ ብቃት (rational and pragmatical mind set) ላይ ለመድረስም የጠራ ራስን የምንመለከትበት መስታወት (self image) ሊኖር ይገባል።

ማንኛውም የፖለቲካ ስብስብ (ፓርቲ ፤ ግንባር ፤ ህብረት ... ወዘተ) የሚቋቋምበት የመጀመሪያው አላማ የዛ ስብስብ ኢሊቶችን የስልጣን ፍላጎትና ጥቅም ለማስጠበቅ እንደመሆኑ የፖለቲካው ኢሊት የራሱን ፖለቲካዊ ጥቅምና ፍላጎት ከህዝብ ከአገር ጥቅምና ፍላጎት አንገዋሎ መለየትና በግልጽ ማስቀመጥ መቻል አለበት።

ለህዝብ መብትና ነጻነት፤ ለአገር እድገት ብቻ የቆመ፤ ምንም የግል ጥቅምና ፍላጎት የሌለው ፖለቲከኛ እሱ delusional ኮምኒስት ብቻ ነው ።ፖለቲከኛ ጻድቅ፤ የፖለቲካ ድርጅት ደግሞ የበጎ አድራጎት ድርጅት አይደሉም መሆንም አይችሉም። ለህዝብ መብትና ነጻነት ብቻ የቆሙና የሚታገሉ የሰብአዊ መብት አስከባሪ ድርጅቶችና ግለሰቦች ብቻ ናቸው። ለአገርም ፍሰሃ ብቻ የቆሙ ኢ-ፖለቲካዊ አገር ወዳድ ዜጎች ብቻ ናቸው።

የህዝብ ዋና ፍላጎቱ ነጻነት - ማለትም ጭቆና እንዲወገድለት ነው። የፖለቲከኛ ዋናው ግቡ የመጨቆኛ መሳሪያውን በእጁ ማስገባት ነው - ስልጣን ነው።

የብዙ ፖለቲከኞች የመጀመሪያው የአዳም ሃጢያት ከዚህ እውነታ ጋር ያለው የከህደት ግኑኝነት ነው። በሌላው በባላንጣ ላይ በጉልህ ማየት የሚቻለውን እውነታ በራስ ውስጥ ለማየት አለመፈለግ የሞራልና የስነ ልቡና ድክመት እንደሆነ ፕሮፌሰር መሳይ ገና ድሮ ከአስር አመት በፊት ለንባብ ባበቃው "From Marxism-Leninism to Ethnicity: the Sideslips of Ethiopian Elitism" በሚለው ጽሁፉ እንዲህ ሲል አብራርቶታል።

> "...It is high time that intellectuals present themselves to the Ethiopian peoples as ordinary persons having specific interests and many limitations. Only thus can they evolve a contractual relationships with the masses whose support they need to defend their interests in the framework of a pluralist society. Only when they admit that they have particular interests can they get out of paternalism by clearly understanding that in defending the interests of the masses they are but defending their own particular interests. This is called general interest and partnership as a result of solidarity being created on the basis of mutual interests and not on the one party granting rights to the other party and deceitfully claiming to be without interest."

ሁሉም በተለያየ መስመርና መዋቅር ስር የተሰለፉት ፖለቲከኞች እኩል የጋራ ባህርያቸው የስልጣን ጥም (ambition) ነው። ይህን ሃቅ በራሳቸው ውስጥ መመልከቱና ተገቢ እውቅና መስጠቱ ራስን ብቸኛ መሲህና ሙሴ አድርጎ የመቁጠሩ የአብዮት ዘመን syndrom እንዲያሽር ይረዳል። ይህን አይነት እውቅና እኔ ህዝባዊ አንተ ጸረ-ህዝብ ፤ እኔ አገር ወዳድ አንተ አገር አፍራሽ ፤ እኔ መልአክ አንተ ሰይጣን የሚለው ጥንፈኛ rehtoric ጋብ እንዲልና በዚህም ይህ አይነቱ rehtoric የሚፈጥረውን መርዛማ የጥላቻ ከባቢ አየር እንዲጠራ እድል ይፈጥራል።

ከራስ አምልኮ self righteousness ጣራ ወርዶ ከ self delusion ተላቆ ለመሰረታዊ ፍላጎት ማለትም - ለስልጣን - ያለንን ፍጹም ታማኝነትን መረዳት መቻል ከአቅማችን አኳያ ፍላጎታችንን ለመመጠንና የሌሎችንም ፍላጎትና አቅም እውቅና ለመስጠት እንድንችል ያደርጋል። ይህም በተራው በጋራ አብሮ መስራት በሚቻልባቸው መስኮች ተቻችሎ አብሮ ለመስራት ፈቃደኝነትን ይቀስቅሳል። በጋራ አብሮ መስራት ደግሞ ቀረቤታና መተማመንን ፤ መተማመን ደግሞ ሁሉንም እኩል የሚያሳትፍ የፖለቲካ ምህዳር ለመቅረጽ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። መሳይ ከበደ "Each camp must come half way so that they all meet where power-sharing arrangement takes form." ሲል ሌላ ሳይሆን ይህንን ማለቱ ነው።

እዚህ ላይ ሊታከል የሚገባው ይህ እውን እንዲሆን ለማስቻል ለዚህ ለውጥ ዝግጁ የሆነ፤ ያለፈ የጥላቻና የቁርሾ ሸክም ከጀርባው ያላዘለ አዲስ fresh ትውልድ በየድርጅቶቹ ውስጥ critical mass ደረጃ ላይ መድረስን ይጠይቃል። በተጨማሪ ከዚሁ ጋር እስካሁን ያለው ችግር ምክንያት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የፈጠሩት ሳይሆን ታሪካዊ መንስኤ ያለው መሆኑንና የትውልዱ የጋራ ድክመት መሆኑን ታሳቢ ባደረገ ግንዛቤና እምነት ላይ የተመሰረተ ተከታታይነት ያለው የይቅርታና የእርቅ ሂደት በጎኑ ያለማቋርጥ ማካሄድን ግዴታ ይላል።

የአብዮተኞች ዘመን የፍጻሜ ደውል ከግዜ ወደ ግዜ እየጎላ ከአድማስ አድማስ እያስተጋባ እነሆ በየቤቱ በር እያንኳኳ ይገኛል።

ሰሚ ያገኝ ይሆን?

....መጪው ግዜ ያሳየናል።

## <u>የአረብ አገሮች አብዮት</u>

በኢትዮጵያ ስለ አብዮተኞች ዘመን ፍጻሜ ከተወሳ ዘንድ በሰፊ የተነገረለትን የአረብ አገሮች አብዮት ማንሳትና መዳሰስ ተገቢ ይሆናል።

የአረብ አገሮች አብዮት በብዙዎች ለረዥም ግዜ ሲጠበቅ የነበረ ክስተት ነበር። እንዴት እንደሚከናወንና ውጤቱም ምን አይነት የጂኦ ፖለቲካል ለውጥ በአካባቢው እንደሚፈጥር የተለያዩ የአፈጻጸም ድራማዎች (scenario) የተጻፉለት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ "Never Quit the Fight" የሚለው የ Ralphs Peters መጽሃፍ በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው።

የአረቦች ጸደይ (Arab Spring) የሚል ቅጽል ያገኘው ይህ የአረብ ህዝቦች አብዮት ልክ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ እንደታዩት የምስራቅ አውሮፓ አገሮች አብዮቶች ልዩ የአለም አቀፍ ፖለቲካ ምክንያት ወይም context ነበረው። የምስራቅ አውሮፓ አገሮች አብዮት እንዲከሰቱ ያስቻለ ቀዳማዊ ሁኔታ እንደነበረ ሁሉ ለአረቦችም አብዮት ተመሳሳይ አለም አቀፍ ቅድመ ሁኔታ አለው።

እንደሚታወሰው ብርቱካንማ፤ ወይንጠጅማ ... ወዘተ የሚል ቅጽል ያገኙት የምስራቅ አውሮፓ አገሮች አብዮቶች ከመከሰታቸው ዋዜማ በአለም አቀፍ የፖለቲካ ስርአት ውስጥ አንድ ልዩ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። ይህም ልዩ ሁኔታ በግዜው የነበረውን የሁለት ዋልታ አለም አቀፍ የፖለቲካ ስርአት ካቆሙት አንዱ ሃያል አገር ከመድርኩ መወገድ ነበር። የአለም አቀፍ የፖለቲካ ስርአቱን ያቆመው አንዱ ዋልታ ሃያል አገር ሶቭዬት ህብረት ሲፈርስ የፈጠረው አለም አቀፍ የፖለቲካ ስርአት ነውጥ እንደ ማእበል ንዝረት (shock wave) ሆኖ በምስራቅ አውሮፓ አገሮች ውስጥ አብዮቶችን ሊቀሰቅስ ችልዋል።

ከታች ያለው የምድር ወለል (Earth crest) ሽግሽግና ፍጭት ከላይ የምናየውን የመሬት መንቀጥቀጥ፤ ሱናሚና የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ እንደሚያስከትል ሁሉ የአለም አቀፍ የፖለቲካ ስርአት ለውጦችም በተመሳሳዩ በአገራት የአብዮት ማእበሎችንና የስርአት ለውጦችን ይቀስቅሳሉ። የአለም አቀፍ የፖለቲካ ስርአት ለውጥ ታሪካዊ ለሆኑ አብዮቶችና የስርአት ማህበር ለውጦች እንደ ቅድመ-ሁኔታ ያገለግላሉ።

አብዮት በመሰረቱ የህዝቦች የነጻነት መንፈስና ስሜት እልህ መገለጫ ፍንዳታ ነው፡፡ የህዝቦች የነጻነት መንፈስና ስሜት ልክ ከመሬት ስር እንዳለ እሳተ ገሞራ ሁልግዜ የጋመና የማይበርድ፤ ሁልግዜ መውጫ መንገድ የሚፈልግ ነው። አብዮት ይመጣል እንጂ አብዮት አይጠራም።ይህን የነጻነት መንፈስና ስሜት የማይንከባከብ ስርአት ባለበት ሁኔታ በበርካታ አገራት በተመሳሳይ ጊዜ አብዮቶች ፈንድተው ለመውጣት የውስጣዊ ስርአት መዳከም ብቻ ሳይሆን ቆሞ የሚደግፈው የአለም አቀፍ ስርአትም መድከም ወይም መውደቅ ቅድመ ሁኔታ ይሻል።

የአረቦች አብዮት ወደ ኢትዮጵያ ይዛመታል ወይስ አይዛመትም የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በአገር ውስጥ ያለው ስርአት የህዝብን የልብ ትርታ እየተከታተለ መልስ ይሻል አይሻም ለሚለው ጥያቄ በአሉታዊ ቢመለስ እንክዋን ይህ የአረብ አገሮችን አብዮት ያስከተለ የአለም አቀፍ ስርአት የለውጥ ሂደት በኢትዮጵያስ ላይ ተመሳሳዩን ተጽእኖ አሳድሮ አብዮት ማስከተል ይችላል ወይ የሚለው ሌላ ጥያቄ ሆኖ ይቀርባል። ይህም ጽሁፍ የዚህን ጥያቄ መልስ ለመዳሰስ ይሞክራል።

ለአረብ አገሮች አብዮት እውን መሆን አሁን በአለማችን ላይ ያለው አለም አቀፍ ስርአት ውስጥ እየተፈጠረ ያለው የለውጥ ሂደት ምንድነው? ይህን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስፈልገውን ንድፈ ሃሳባዊ መንደርደሪያ በመጀመሪያ እንመልከት።

ካፒታሊዝም ተጸንሶ ከተወለደበት ከአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከሱ ጋር አብሮ የተፈጠረው ግሎባላይዜሽን መላው አለምን እያቀራረ ዛሬ የምንገኝበት ትልቅ የውህደት ደረጃ ላይ አደርስዋል። በካፒታሊስት ስልተ-ምርት አደረጃጀት መሰረት ለጥሬ እቃ፤ ለገበያና ለርካሽ ጉልበት የሚያደርገው ሩጫና ፉክክር በተፎካካሪውቹ አገራት መሃል የማያቋርጥ የጦርነትና የስምምነት ኡደቶች እንዲካሄዱ አድርግዋል።

በጦርንቱ አሸናፊ ሆኖ የሚወጣው አገር የራሱን ጥቅም የሚያስጠብቅ ስምምነትን አውጥቶ ተሸናፊዎቹን ሲያስፈርም ያ ስምምነት የአለም አቀፍ ፖለቲካ ስርአት መሰረት ይሆናል። ከጊዜ ጋር አሸናፊው ሃያል አገር ሲደክም ወይም ሌላ ተፎካካሪ ጠንክሮ ሲውጣ ሌላ አዲስ ጦርነት፤ አዲስ አሸናፊ ሃያል አገር፤ ሌላ አዲስ ስምምነትና ሌላ አለም አቀፍ ስርአት እየተተካካ ዛሬ አምስተኛው የኡደት ሂደት ላይ ይገኛል።

እንዲህ እያለ ከአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ አሁን የምንገኝበትን ጨምሮ አምስት አለም አቀፍ ስርአቶች በታሪክ የተመዘገቡ ሲሆን በሰንጠረዥ ውስጥ እንዲህ ተካተዋል።

**The Long Cycle: Basic Facts**

| World Power | Formative Global onflict | Legitimizing Settlement | Institutional Innovations | Landmarks of Descent |
|---|---|---|---|---|
| Portugal | Treaty of Tordesillas (1494) | Treaty of Tordesillas (1494) | Organization of exploration and discovery<br>Global Network of bases Carreira de India<br>Antwertp entrepot | Spanish annexation (1580)Wars of Religion 'Sovereignty (1576) |
| Netherlands | Spanish Wars (1579-1609) War of Dutch Independence | 1609 welve-year Truce with Spain | 'Mare librum." Free trade<br>Amsterdam Bank, Bourse, Grain Exchange<br>United East India Company | Wars with England<br>War with France (1672-78)<br>The English Revolution |
| Great Britain (1st) | French Wars (1688-1713) (Louis XIV) | 1713 Treaty of Utrecht | Command of the Sea (Navy) European Balance of Power Indirect control of world trade Bank of England, National debt | Independence of the U.S.<br>Partitions of Poland French Revolution |
| Great Britain (2nd) | French Wars (1792-1815) | 1814-15. Paris, Vienna | Naval command: antislavery Free trade: gold standard.<br>Industrial Revolution Independence of Latin America<br>'Opening' of China and Japan | Anglo-German naval race<br>Imperialism Russian evolution<br>Great Depression |
| U.S | German Wars (1914-18; 1939-45 | 1919.Versailles<br>1944.Yalta. San Francsco. Postdam<br>1991 Washing. consensu | United Nations Strategic Nuclear deterrence<br>Multinational corporations Decolonization Space Exploration | -2008 Financi al crise -Arab uprisin g |
| Who? China ??? | ???? | ??? | ??? | |

(George Modelski: The Long Cycle of Global Politics and the Nation-State)

እያንዳንዱ የአለም አቀፍ ስርአት ኡደት በጦርነት ማግስት ተጀምሮ በጦርነት የሚያልቅና እድሜውም ቢያንስ ሶስት ትውልዶችን የሚያካትት ነው። በዚህም ግዜ ውስጥ የአለም አቀፉ ስርአት ሁለት ደረጃዎችን የሚያልፍ ሲሆን የመጀመሪያው እርከን ሃያሉ አገር (global power) አዲሱን ስርአት በመላው አለም የማስፈን ግንባታ የሚካሄድበትና የሚቆጣጠርበት ይሆናል። ሁለተኛው የሂደት ደረጃው ደግሞ እየደከመና የቋጠረው እየተፈታ የሚመጣበት ግዜ ይሆናል።

የአለም አቀፉ ስርአት በሁለተኛው የእድገት ደረጃው መጨረሻ ላይ ሲደርስ ማለትም ሃያሉ አገር መዳከም ሲጀምርና የአለም አቀፉ ስርአት መሰነጣጠቅ ሲከተል አብዮቶች በየአካባቢው እንደ አሸን መፍላት አለም አቀፍ ሽብርተኝነት መስፋፋት ይጀምራሉ። እነኝህ አብዮቶች

የሚከሰቱባቸው አገራት ደግሞ የአለም አቀፉ ስርአት ደካማ ቀለበቶች በሆኑት ማለትም በስርአቱ ዘመን ክፉኛ የተገፉና የተበደሉ አገራት ውስጥ ሲሆን የስርአቱንና የሀያል አገሩን ድክመትና ውድቀት ከማንም የበለጠ በቶሎ የሚሰማቸውና ፈጥነውም የ ሚነሱት እነኝህ አገሮች ናቸው።

አሁን ወዳለንበት ስርአት ላይ ስናተኩር ከአንደኛው አለም ጦርነት ማግስት የአሜሪካ የበላይነት እውን ከሆነና በሁለተኛው አለም ጦርነት ፍጻሜ በአሜሪካ መሪነት የያልታ ስምምነት ሲፈረም አዲስ አለም አቀፍ የፖለቲካ ስርአት ይመሰረታል።

> "The first German war gave a provisional answer, and its outcome seemed to assure the United States a leading role in the settlement of the peace and in the laying of the foundations of the new international order. But President Wilson was repudiated at home, and the United States neither took up the position that was its own for the taking nor offered an alternatve scheme for world order. The resulting vacuum of authority attracted another challenge and another cataclysmic clash. The two great wars of the the twentieth century (called the First and Second World Wars confusingly because, as we have shown, the world has known world wars in several earlier cycles too) may be seen as one generation-long period of global conflict forming the world order that emerged in 1945."
> (George Modelski :The Long Cycle of Global Politics and the Nation-State)

ሆኖም የአሜሪካ ፍጹም የበላይነት የተረጋገጠበትና አሁን የምንገኝበትን አለም አቀፍ ስርአት በመላው አለም ገዥ መሆን የጀመረው ከሶቭየት መፍረስ ጋርና የዋሽንግተን ኮንሴንሱስ የኢኮኖሚ መርህ ሲፈበረክ ይሆናል።

አሁን ያለንበት ነጥብ የአለም አቀፉ ስርአት ሂደት ሁለተኛ የእድገት ደረጃ ላይ እንደመሆኑ የአሜሪካ እንደ ብቸኛ አለም አቀፍ ሃያልነት ማቆልቆል የጀመረበት፤ ከዚህም ጋር አብሮት የአለም አቀፍ ስርአት እየተዳከመ ያለበት፤ አዳዲስ ተፎካካሪዎች (ቻይና፤ ህንድ....ወዘተ) ለአዲስ ሚና ራሳቸውን እያዘጋጁ የሚገኙበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን።

> "..Significantly, in 2008, the U.S. National Intelligence Council admitted for the first time that America's global power was indeed on a declining trajectory. .... Under current projections, the United States will find itself in second place behind China (already the world's second largest economy) in economic output around 2026, and behind India by 2050. Similarly, Chinese innovation is on a trajectory toward world leadership in applied science and military technology sometime between 2020 and 2030." (CBS News, December 6, 2010)

ወደተነሳንበት ወደ አረቦች አብዮት ስንመለስ:-

በአሜሪካ የሚመራው አለም አቀፍ ስርአት ውስጥ ደካማ ቀለበቶች ማለትም በስርአቱ የተገፉ ወይም የመጨረሻ ተጠቃሚዎች የሆኑት አረቦችን ጨምሮ የአፍሪካ የደቡብ አሜሪካና የኤስያ ድሃ አገራት ህዝቦች ናቸው። በመሆኑም አብዮትና አለም አቀፍ ሽብርተኝነት ቢነሳ ሊነሳና ሊቀጣጠል የሚችልባቸው ምቹ መደቦች (fertile ground) እነኝህ አካባቢዎች ይሆናሉ ማለት ነው።

በነኝህ አገራት የሚገኙት ስርአቶችም የአለም አቀፉ ስርአት አካልና የገዥ ክፍሎችም በሃያሉ አገር ድጋፍና ፈቃድ የቆሙ እንደመሆናቸው የሚነሱት አብዮቶችና አለም አቀፍ ሽብሮች በአለም አቀፉ ስርአትና በጠባቂው ሃያል አገር ላይም የተነጣጠሩ ይሆናሉ።

ሃያሉ አገር ሲዳከምና አለም አቀፉ ስርአት መናጋት ሲጀምር በነኝህ አገራት ለአብዮት መፈንዳት ቀዳዳ መከፈት ይጀምራል። የአሜሪካ የኢኮኖሚ እድገት ማቆልቆል ብቻ ሳይሆን የተቀናቃኝ አገራት ፈጣን እድገት ልዩነቱን ማጥበቡ፤ በአሜሪካ የጀመረው የፋይናንስ ቀውስ መዘዝ ያስከተለው አለም አቀፍ ቀውስና ውግዘት፤ ከአንድ አስርተ አመታት በላይ እየተካሄደ ያለው የአለም አቀፍ ጸረ-ሽብርተኝነት ጦርነት ያስከተለው የዲፕሎማሲ የሞራልና የአቅም ኪሳራ ሁሉ ተደራርቦ አሜሪካ የሃያል አገር ሚናዋ ድክመት በሁሉም ዘንድ እንዲታይና እንዲዳሰስ አድርጓል።

ይህ ሁኔታ ለሁሉም አገሮች እኩል ሆኖ የአረቦች አብዮት ከሌሎች አገራት ከማንም ቀድሞ መፈንዳት የጀመረበት አንድ ሌላ ልዩ ምክንያት አለው። ይህም የአረብ ህዝቦች ከአለም አቀፉ ስርአት እንደ ሌሎቹ ተጠቃሚ አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፉ ስርአት የተጠቂነትና የተገፊነት ስሜትም ያተርፉ በመሆናቸው ነው። በፓሌስቲኖች ላይ የደረሰውና የሚደርሰው ግፍና ሰቆቃ አረብ ህዝቦች በራሳቸው ላይ የደረሰ በደልና ግፍ አድርገው የሚቆጥሩት ሲሆን ለዚህም ዋና ተጠያቂ አድርገው የሚያዩት የእስራኤል ቋሚ ጠብቃና ደጋፊ አሜሪካና ዲክቴት የሚያደረገው አለም አቀፍ ስርአቱን ነው።

በዚህም ምክንያት የአሜሪካና የአለም አቀፉ ስርአት ድክመት ከማንም በላይ የሚሰማቸውና ፤ በቋፍ ላይ የሚገኙ ህዝቦች መሆናቸው ማናቸውንም ቀዳዳና አጋጣሚ በመጠቀም የአሜሪካና የአለም አቀፉ ስርአት ጓንት ሆነው የሚያገለግሉትን መንግስቶቻቸውን አሽቀንጥሮ ለመጣል የተዘጋጁ አድርጓቸዋል። ራሱን ያቃጠለው ቱኒሲያዊ የተሰፉ ማጣትና የእልህ ስሜት በአረብ አገር ህዝቦች ውስጥ ለረዥም ጊዜያት ታምቆ የቆየውን ስሜት የሚያንጸባርቅ መግለጫ፤ በእስራኤልና በአሜሪካ የሚደርስባቸው ውርደትና ሰቆቃ የሚገልጽ ስሜት ነበር። ለዚህም ነው ያ የተጠቂነት ስሜት በመላው የአረብ አገራት ከዳር እስከዳር ያስተጋባውና resonance ያገኘው።

እዚህ ላይ አሜሪካ በአረብ አገራት የሚነሱትን ህዝባዊ አብዮቶች ሁሉንም ትደግፋለችን የሚል ጥያቄ መነሳቱ ግድ ይላል? አሜሪካ እንደ አለም አቀፉ ስርአት ቁንጮ የmonopoly rent ተቀባይ አገር ናት። ይህም ማለት አሜሪካ ያላት አለም አቀፍ የመሪነት ቦታና ከሱም ጋር ተያይዞ

የሚከተለው የሃያል አገር (global status) አንጻራዊ ነጻነት ነው። ይህ ቦታም አሜሪካን የአለም ፖሊስና ዳኛ ሚና እንድትጫወት ግድ ይላል። ጦርነት፤ ቀውስና አብዮት በሚነሱባቸው ስፍራዎች ሁሉ የራስን ጥቅምና አለም አቀፍ ስርአቱን በማያናጋ መልኩ እንዲፈቱ ጣልቃ መግባት የአሜሪካ ድርሻ ሆኖ ይጠብቃል። ሆኖም የአሜሪካን ጥቅም ቀጥተኛ አደጋ (immediate risk) ሊደርስበት በሚችልባቸው አገሮች ከህዝብ አብዮት ይልቅ አገልጋይ ስርአቱን እንደምትመርጥ ምንም ጥርጥር አይኖረውም ።

ከአረቦቹ በተለየ በአፍሪካና በመሳሰሉት አገራት ግን ይህ የአለም አቀፍ ስርአት የመናጋቱ ንዝረት በቅጡ ደርሶ አብዮት ለመቀስቀስ አልበቃም። አብዮት ለማምጣት ግሎ አላሰማም። ለዚህም ምክንያቱ እነኚህ አገራት የአለም አቀፉ የፖለቲካ ስርአትና ከሱም ለውጥ ጋር ያላቸው ቀጥተኛ የተጽዕኖ ግንኙነት የላላና ጠብቆ የገጠመ ስለላልሆነም ጭምር ነው። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነው የ2008 የፋይናንስ ቀውስ አፍሪካ አገሮችን በርቀትና በጨረፍታ ነክቶ ማለፉ ከፖለቲካው ስርአትም ጋር ያላቸውን ሰፊ ርቀት የሚለካ ነው።

ሆኖም ግን የማይቀረው የአለም አቀፍ የፖለቲካ ነውጥ ፍጥነት ሲቀየርና የአፍሪካና የመሳሰሉትአገሮች ከአለም አቀፉ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ስርአት ጋር ያላቸው ትስስር ጠብቆም የህዝቡን ህይወት መለውጥ ካልቻለ የአረቦች አይነት ወይም ለየት ባለ መልክ የህዝብ መነሳሳት በበርካታ አገሮች በአንድ ግዜ ሊከናወን ይችል ይሆናል። ግዜውን የሚወሰነው ይህ ሂደት ሲሆን ቢያንስ ከ አስር እስከ ሃያ አመት ያህል ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

ከዚህ በመነሳት ኢትዮጵያም ውስጥ ያለው ስርአት የህዝብን ትርታ እየተከታተለ የማያዳምጥና መልስ የማይሰጥ ቢሆን እንኳን የግብጾችን አብዮት የጫረው ውጭያዊ ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ ተመሳሳዩን ለማድረግ ዛሬ አቅሙ ውሱን መሆኑን ያሳየናል። ለዚህም ነው የግብጽን አብዮት ባለንበት ወቅታዊ ሁኔታ ወደ ኢትዮጵያ ትራንስፖርት ማድረግ የማይቻለው:: አብዮት ኢትዮጵያ ውስጥ ከተከሰተ ከጋርዮሽ አረባዊ አብዮት ጋር የማይዛመድ ኢትዮጵያዊ አብዮት ነው የሚሆነው።

ዋናው ነጥብ- አብዮት ይመጣል እንጂ አይሰራም። ራሱ በራሱ ይፈነዳል። የአብዮት ፍንዳታ ደግሞ በራሳችን ታሪክ እንደምናውቀው ሁሉም ወደሚመኘው ግብ ማድረሱን ማንም ደፍሮ በእርግጠኝነት መናገር አይችልም ። አልፎም ወደ ማይጠብቅና ወደማይፈልግ አቅጣጫ ላለማምራቱም ዋስትና የለም። የህብረተሰቡን ስብጥራዊ ማንነት፡ የቀጠናውን አስጊነት ታሳቢ በማድረግ የአገርን እጣ ፋንታ የአብዮት ምርኮኛ ለማድረግ መሞከር ለአገር ያለንን ፍቅር የሚጻረር ነው። በሁነቶች ላይ ያልተመሰረተ በእቅድና በፕላን ውጤቱ የሚተነበይ ግብር ማሰብ ለአገር የበለጠ ፋይዳ ይኖረዋል።

ልዩነቶችን አቻችሎ አንድነትን ማቀድና መተግበር ይቻላል ያም ለአገር ጠቃሚና ውጤቱንም በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል ። ውጤቱም ከአስርና ሃያ አመታት በሁዋላ ኢትዮጵያን ካደጉት አገሮች ተርታ መሃል ገብታ የአዲሱ (multi-polar) አለም አቀፍ ስርአት ፈጣሪዎች አንዱ ዋልታ መሆን መብቃትዋ ነው ።

የዛን ግዜም አብዮት የታሪክ መዝገበ-ቃል ሆኖ ይቀራል ።

ፍቅረ ህዝብ አሸናፊ

University of Utah

የዚህን ጽሁፍ አቅራቢ (በፍቃዱ ወ/ ገብርኤል) - በዚህ ኢ-ሜይል አድራሻ ማግኘት ይቻላል fekerehezb@live.com